# ኢትዮ-ቻምበር በዚህ ሰሞን
# Ethio-Chamber Alert

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ የዜና መጽሄት

ቁጥር 160

ሰኔ 1-15/2010 ዓ.ም.

## በውስጥ ገጾች

2ኛው የቢዝነስ ሩጫ ... ገጽ... 2

ሴት ነጋዴዎች ... ገጽ...2

... በድጋፍ ሰልፍ የተጎዱ ወገኖችን ... ገጽ... 3

የመንግሥት ባንኮች ወደ ግል ...
https://www.ethiopianreporter.com/article/11518 ገጽ... 3

የአሜሪካ ዲፕሎማቶች በኢትዮጵያ...
https://www.ethiopianreporter.com/article/11517 ገጽ... 3

የቱርክ ኩባንያ በትግራይ ...
https://www.ethiopianreporter.com/article/11503 ገጽ... 3

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ማዕከል

አድራሻ፡- +251-115-31-10-15

ዋና አዘጋጅ፡- ደበበ አበበ

አዘጋጆች፡- ዮሴፍ ተሾመ
ጥበቡ ታዬ

ካሜራ፡- ያሬድ አባቡ

ፕሮቶኮል፡- ሲሳይ አስታጥቄ

**አድራሻ**

ስልክ፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ኢሜል፡- ethchamb@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

# 2ኛው የቢዝነስ ሩጫ በድምቀት ተካሄደ




‹‹ለኢንዱስትሪ ልማት እንሩጥ!›› በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀው 2ኛው የኢትዮጵያ የቢዝነስ ሩጫ እሁድ ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም. በደመቀ ሁኔታ ተከበረ፡፡ መነሻውንና መድረሻውን መስቀል አደባባይ በማድረግ 5ኪ.ሜ. በሚሸፍነው በዚህ ሩጫ ላይ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት፣ ከፌዴራል ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን፣ ከሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ፣ ከሰንሻይን ኮንስትራክሽን፣ ከኢትዮ ፓወር ኢንጂነሪንግ እና ከበርካታ የተለያዩ የግል ድርጅቶች የተውጣጡ ከፍተኛ አመራሮችና ሠራተኞቻቸው እና ማህበረሰቡ ተሳትፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ የቢዝነስ ሩጫ ባለቤትና አዘጋጅ የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሲሆን የዝግጅቱ ዓላማ በሀገሪቱ ስላለው የኢንዱስትሪ ልማት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥና የግሉ ዘርፍ (የንግዱ ማህበረሰብ) በኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ የሚኖረውን ሚና ለማሳደግ እንደሆነ ታውቋል፡፡

በዕለቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) እንደተናገሩት ምክር ቤቱ በአዋጅ ከተቋቋመባቸው ተግባርና ኃላፊነቶች ውስጥ አንዱ ንግድና ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ በማገዝ የግሉ ዘርፍ በሀር ኢኮኖሚ ውስጥ የመሪነት ሚናውን እንዲጫወት ማስቻል ነው ካሉ በኋላ ይህ 2ኛው የኢትዮጵያ የቢዝነስ ሩጫም ንግድና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት የግሉ ዘርፍ በኢንዱስትሪው ልማት ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ የሚደረገው ጥረት አንዱ አካል ነው፡፡

የዕለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት የፌዴራል የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዶ/ር አምባቸው መኮንን በመክፈቻ ንግግራቸው የ2ኛው የኢትዮጵያ የቢዝነስ ሩጫ አዘጋጅ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አመራሮችና ሠራተኞች የኢትዮጵያ ቢዝነስ ሩጫ ጠንሳሾችና ጀማሪ ባለቤቶች በመሆናችው አክብሮታቸውን በምስጋና ከገለጹ በኋላ ‹‹ለኢንዱስትሪ ልማት እንሩጥ!›› በሚል መሪ ቃል በተለይ ደግሞ በዘላቂ አረንጓዴ ማኑፋክቸሪንግ (sustainable manufacturing) ላይ ትኩረት ያደረገው ይኸው ሩጫ ሀገራችን ወደ ኢንዱስትሪ ልማት በምታደርገው ሽግግር ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ብለዋል፡፡

በዕለቱ በዝግጅቱ ላይ የተገኙት የአውሮፓ ህብረት ተወካይ ሚ/ር ጆን ህብረቱ የሀገሪቱን የኢንዱስትሪያላይዜሽን ስትራቴጂ እንደሚደግፍ እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

የውድድሩ ተሳታፊወዎች ስፖርት በባህሪው ከተለያዩ አካባቢ የሚመጡ ቡድኖችን በማቀራረብ አንድ ዓይነት ስሜት እንዲጋሩ የማድረግ ኃይል እንዳለው በመግለጽ የዛሬው የቢዝነስ ሩጫ ከዚህ አንፃር በንግዱ ማህበረሰብ መሃል ያለው ግንኙነት የበለጠ እንዲጨምርና ልምዳቸውን እንዲጋሩ ያስችላል ብለዋል፡፡ ዝግጅቱ በቀጣይ የግሉ ዘርፍ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ሊያበረክት በሚችለው ድርሻ ላይ ትኩረት ለማድረግ እንደሚያስችለውም እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

2ኛውን የቢዝነስ ሩጫ ዓባይ ባንክ፣ ደርባ ሲሚንቶ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ቤካ ጀነራል ቢዝነስ፣ ሮሃ ፓክ ኃ.የተ.የግ ኩባንያ፣ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት፣ ጎመጁ ኦይል ኢትዮጵያ፣ አሀዱ ኃ.የተ. የግል ኩባንያ፣ ሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ፣ ዲ.ኤች. ገዳ፣ ኔትኮ ትሬዲንግ ኃ.የተ. የግል ኩባንያ፣ ፀሐይ ኢንዱስትሪ አክስዮን ማኅበር፣ ጣምራ ቴክኖፓኬጂንግ ኃ.የተ. የግል ማኅበር፣ እና ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት በገንዘብና በቁሳቁስ ድጋፍ ያደረጉ ሲሆን፣ በቀጣይ ምክር ቤቱ ለሚያከናውናቸው የልማት ተግባራት አጋርነታቸው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ኢንጂነር መልአኩ ‹‹ባለፈው ዓመት በ1ኛው የቢዝነስ ሩጫ ላይ የተሳተፋችሁ የኩባንያ ባለቤቶችና ሠራተኞች በመጀመሪያውና በታሪካዊው ሩጫ ላይ ያሳያችሁትን አብሮነትና ትብብር ለመድገም ዛሬም ከኛ ጋር ስለሆናችሁ ደስታዬ እጥፍ ድርብ ነው፡፡›› ሲሉም ለተሳታፊ ድርጅቶች ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ምክር ቤቱ ይህንን የጎዳና ላይ ሩጫ ያዘጋጀው ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከአውሮፓ ህብረትና ከተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (ዩኒዶ) ጋር በመተባበር ዝግጅቱን በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቀ ሲሆን ለአሸናፊ ተወዳዳሪዎችና ድርጅቶቻቸው ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

## ሴት ነጋዴዎች በስልጠናና በፋይናንስ አቅማቸው ሊገነባ ይገባል ተባለ






የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ነጋዴ ሴቶች በቢዝነስ ዕንቅስቃሴዎቻቸው *በሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶችና መፍትሄዎቻቸው እንዲሁም ባሏቸው እድሎች ዙሪያ የመከሩበትን* የመጀመሪያው የኢትዮ-ቻምበር ነጋዴ ሴቶች ፎረም ሰኔ 15 ቀን 2010 ዓ.ም በግዮን ሆቴል አካሄደ።

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) እንደተናገሩት በኢትዮጵያ ሴቶች በማህበረሰቡ ብሎም በሀገር ደረጃ ሁለንተናዊ ሚና ያላቸው ከመሆኑ አንፃር በሙያዊ ስልጠና እና በፋይናንስ ቢደገፉ የራሳቸውን ገቢ ከማዳበር ባሻገር የሀገሪቱን ኢኮኖሚም በማሳደግ ረገድ የሚኖራቸው ተሳትፎ የላቀ ነው፡፡ ሴቶች በቢዝነሱ እንቅስቃሴ እንዲጎለብቱና ተጠቃሚ ሊሆኑ በሚችሉባቸው አማራጮች እንዲሁም በሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ እየተገናኙና ለሚመለከታቸው እያቀረቡ በምክክር እንዲፈቱ ለማድረግ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ፕሬዚደንቱ ጨምረው አሳስበዋል፡፡

የዕለቱ የክብር እንግዳ የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ ክብርት ወ/ሮ ሂሩት ዘመነ በመክፈቻ ንግግራቸው ላይ እንደተናገሩት የሴቶች በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን ለሴቶቹ ብቻም ሳይሆን በሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ የጎላ ድርሻ ያለው በመሆኑ ሴቶች ተገቢው እገዛና ድጋፍ ካልተደረገላቸው እንደ ሀገር ዕውነተኛ የሆነ ውጤት ማስመዝገብ አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት መንግሥት ለፆታ ስብጥር በሰጠው ልዩ ትኩረት በፓርላማው ውስጥም ሆነ በከፍተኛ የመንግሥት አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ በእጅጉ መጨመሩን ሚኒስትር ደኤታዋ ገልጸዋል፡፡ በኢኮኖሚው መስክም ቢሆን በርካታ አንጋፋ ሴቶች እየታዩ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶችን አቅም በማብቃት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖራቸውን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማጎልበት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያቀፈ የትብብር ማዕቀፍ (collaborative framework) እንደሚያስፈልግ በውይይታቸው ወቅት ተገልጿል፡፡ ማዕቀፉ ነጋዴ ሴቷ ያሉባትን የፖሊሲ፣ የሎጂስቲክስ፣ የፋይናንስና ሌሎች ተግዳሮቶች በግልጽ በመለየትና የአቅም ግንባታና የሥልጠና ሁኔታዎችን በማመቻቸት የነጋዴ ሴቷን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት እንደሚያግዝ ታምኖበታል፡፡

የትብብር ማዕቀፉን ሰነድ ዝግጅት በተመለከተም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከነጋዴ ሴቶች ማኅበራት፣ ከሴት የኩባንያ ባለቤቶችና ከሚዲያ አካላት የተወከሉ አካላት ከምክር ቤቱ ጋር በጋራ እንደሚሠሩም ታውቋል፡፡

የምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮችና የመንግስት ሀላፊዎች፣ *የነጋዴ ሴቶች* ፣ እንዲሁም ከአጋር አካላት የመጡ በርካታ ተሳታፊዎች በውይይቱ ላይ የተገኙ ሲሆን መልካም ተሞክሮ ያላቸው ነጋዴ ሴቶች የተጓዙበትን ውጣ ውረድና ስኬቶቻቸውን አካፍለዋል፡፡

## የምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች በድጋፍ ሰልፍ የተጎዱ ወገኖችን ጎበኙ





ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በእስካሁን የሃላፊነት ቆይታቸው ላስመዘገቡት ውጤት እውቅና ለመስጠት እና ለመደገፍ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. በተካሄደው ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ በተፈፀመው የሽብር ድርጊት የተጎዱ ዜጎችን የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድና የማኔጅመንት አባላት በጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል በመገኘት ሰኔ 18 ቀን 2010ዓ.ም. ጎበኙ።

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ዶ/ር አይናለም አባይነህ እንደተናገሩት በሀገሪቱ መሪዎች የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ በመደገፍ ዜጎች ስሜታቸውን በጋራ በመግለፅ ላይ ባሉበት ሁኔታ እንደዚህ አይነት ጉዳት የደረሰባቸው አሳዛኝ ቢሆንም ፍቅራቸውን፣ አንድነታቸውንና አጋርነታቸውን ለማሳየት ያደረጉት መስዋዕትነትና ተጋድሎ በመሆኑ ጀግና ያስብላቸዋል፡፡ ዶ/ር አይናለም ጨምረው እንደገለፁት የተጎዱ ወገኖችን በማገዝና በመርዳት ከጎናቸው ለመቆም እንዲሁም ሆስፒታሉ የተደራጀ ባለመሆኑ በቁሳቁስ ለማሟላት የንግዱ ማህበረሰብ አቅም በፈቀደ ሁሉ የበኩሉን ያደርጋል፡፡ የንግዱ ማህበረሰብና መላው የኢትዮጵያ ዜጎች የሀገሪቱን ሰላምና አንድነት ለማጠናከር ደማቸውን እየለገሱና የሚችሉትን ሁሉ እያደረጉ በመሆናቸው እንዲሁም የሆስፒታሉ ሀኪሞችና የጤና ባለሙያዎች ለተጎጅዎች እያደረጉ ላሉት ሙያዊ ርብርብና እንክብካቤም ዶ/ር አይናለም አመስግነዋል፡፡

ሆስፒታሉ በድጋፍ ሰልፉ ላይ ከተጎዱት ዉስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን ተቀብሎ አስፈላጊውን የህክምና እርዳታና እንክብካቤ እያደረገላቸው እንደሆነ ታወቋል፡፡

## የመንግሥት ባንኮች ወደ ግል እንዲዛወሩ ፖሊሲም እንዲቀየር የሚጠይቁ ሐሳቦች

የመንግሥት የፋይናንስ ተቋማት በለውጥ ሒደት ላይ ስለመሆናቸው ከሰሞኑ የተደረጉ የአመራሮች ለውጦች ወይም ሽግሽጎች አመላካች እየሆኑ ነው፡፡ የፋይናንስ ተቋማቱ የአመራር ለውጥ በአገሪቱ ዋና ዋና የሚባሉ ባንኮች ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡

የአመራር ለውጡ ባንኮቹን በበላይነት ይመሩ በነበሩ ግለሰቦች መነሳት ላይ ሳይወሰን፣ የተቋማቱንም አሠራሮች በአዳዲስ ለመተካት እንደተፈለገ ይነገራል፡፡ ከሰሞኑ ከተደረጉ የአመራር ለውጦች ውስጥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ለ13 ዓመታት ሲመሩ የነበሩትን አቶ ተክለ ወልድ አጥናፉን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በፋይናንስ አማካሪነት በመመደብ በቦታቸው አዲስ ገዥ ተተክቷል፡፡ ከዚህ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥና ዋና ኢኮኖሚስት የነበሩትን ዮሐንስ አያሌው (ዶ/ር) ወደ ኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተርነት እንዲዛወሩ መደረጉ ይታወሳል፡፡

ይህ የአመራሮች ለውጥ በብሔራዊ ባንክ ውስጥ በሚገኙ ቁልፍ የሥራ መደቦችም ውስጥ ሊቀጥል እንደሚችል በርካቶች እምነቱ አላቸው፡፡ የብሔራዊ ባንክ ቦርድ አመራር አባላትም በአዲስ እንደሚተኩ ይጠበቃል፡፡ በዘርፉ ሥር ነቀል ለውጥ ሊደረግ እንደሚችል የሪፖርተር ምንጮች የገለጹ ሲሆን፣ ከብሔራዊ ባንክ በተጨማሪ የአገሪቱ ትልቁ ባንክ በሆነው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በኢትዮጵያ ልማት ባንክም የአመራሮች ለውጥ ይደረጋል ብለዋል፡፡ (ሪፖርተር ጋዜጣ እሁድ ሰኔ 17 ቀን 2010) ለተጨማሪ ማብራሪያ ከታች ያለውን ሊንክ ይጫኑ

## የአሜሪካ ዲፕሎማቶችና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ስለተወሰዱ ጅምር የለውጥ ዕርምጃዎች ይናገራሉ

በኢትዮጵያ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ የአሜሪካ ኩባንያዎችና ዲፕሎማቶች በመንግሥት እንደሚወሰዱ ይፋ የተደረጉ የለውጥ ዕርምጃዎች ተስፋ እንዳሳደሩባቸው ገለጹ፡፡

በአሜሪካ ኤምባሲ አዘጋጅነት የተሰናዳው የንግድ ውይይት ሐሙስ፣ ሰኔ 14 ቀን 2010 ዓ.ም. በተካሄደበት ወቅት እንደተገለጸው መንግሥት ይፋ ያደረጋቸው የለውጥ ዕርምጃዎች ለአሜሪካ ኩባንያዎች ብቻም ሳይሆን፣ ለግሉ ዘርፍ ማደግ የሚያስፈልጉና ሲጠበቁ የነበሩ መሆናቸውን በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ማይክል ሬይነር አስታውቀዋል፡፡(ሪፖርተር ጋዜጣ እሁድ ሰኔ 17 ቀን 2010) ለተጨማሪ ማብራሪያ ከታች ያለውን ሊንክ ይጫኑ

https://www.ethiopianreporter.com/article/11517

## የቱርክ ኩባንያ በትግራይ ክልል የኢንዱስትሪ ፓርክ ሊገነባ ነው

በቱርክ ፕሬዚዳንት ረሲፕ ጠይብ ኤርዶጋን ቀጥተኛ መመርያ የቱርክ ግዙፍ ኩባንያ ተርክሽ ሆልዲንግ ኤኤስ፣ በትግራይ ክልላዊ መንግሥት ግዙፍ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሊገነባ መሆኑ ታወቀ፡፡

የተርክሽ ሆልዲንግ ኩባንያ ኃላፊዎች ከትግራይ ክልል ከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር በጉዳዩ ላይ መነጋገራቸውና ለፕሮጀክቱ 300 ሔክታር መፈቀዱ ታውቋል፡፡(ሪፖርተር ጋዜጣ እሁድ ሰኔ 17 ቀን 2010) ለተጨማሪ ማብራሪያ ከታች ያለውን ሊንክ ይጫኑ

https://www.ethiopianreporter.com/article/11503

## 2nd Ethiopian Business Run Colorfully Celebrated



The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), in partnership with Federal Ministry of Industry (MoI), European Union, and United Nations Industrial Development Organization (UNIDO) organized the 2nd Ethiopian Business Run which was colorfully celebrated on Sunday 17th June of 2018 here in Addis.

On the road race which started and ended at Meskel Square of Addis Ababa, covering 5k.m. participants comprised from various public organizations such as Ministry of Industry (MoI), Ethiopian Investment Commission (EIC); international organizations such as European Union and UNIDO; Federal Metal and Engineering Corporation, Medroc Technology Group, Ethio Power Engineering, Sunshine Construction, among others, participated.

The event was intended and organized to achieve the objective of raising the public awareness on the country's course of industrialization and promote the role and engagement of the business community in the industry sector.

In his welcoming speech, Melaku Ezezew (Eng.), President of ECCSA, stating that one of the duties and responsibilities of the Chamber is promoting trade and investment and enhancing the capacity of the private sector towards such responsibility so as to play a leading role in the national economy, he emphasized that this business run is part of such endeavors.

The guest of honor, Minister of Ministry of Industry (MoI), Dr. Ambachew Mekonnon, in his opening speech said the Ethiopian Business Run is part of the national endeavors being made towards industrialization. Besides, he also forwarded his compliments to ECCSA, the organizer of the event for the initiation.

Country representative of the European Union, Mr. John, also reflected the interest of EU in supporting the country's industrialization endeavors.

Abay Bank, Derba Cement, Ethiopian Air Lines, Beaka General Business, Roha Pack PLT P. Company, Ethiopian Insurance Organization, Gomeju Oil Ethiopia, Ahadu PLT Company, Medroc Technology Group, D.H. Geda, NETCO Trading, Tsehay Industrial Share Company, Tamra Techno packaging, and Fana Broadcasting Corporate (FBC) sponsored the event.

Champion organizations and individuals of the 2nd Ethiopian Business Run were awarded Trophy of encouragement and participation; partners and sponsors also received an award of appreciation and compliments.

## 1ST Ethio-Chamber "Women in Business" Forum Organized





The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) organized the "1st Ethio-Chamber Women in Business forum" and discussed on the major challenges and opportunities of women manufacturers on June 22, 2018 at Ghion Hotel, Addis Ababa.

In his welcoming speech, Melaku Ezezew (Eng.), President of ECCSA, said since the women's role in the national development endeavor, it has become significantly essential to provide them as equal technical and financial support as it is to men. Such kinds of consultations have also to be strengthened on a sustainable basis so as to enhance the economic involvement of women, he added.

Her Excellency Mrs. Hirut Zemene, Deputy Minister of Federal Ministry of Foreign Affairs (MoFA), in her opening remark said that we couldn't bring a real output at national level without effective participation of women in the political, social and economic sphere in the country. "Therefore," said the Deputy Minister, "the government, giving due consideration to the participation of women in the national agenda, the number of women parliamentarians and women at higher executive level is now increasing." The involvement of women in the economy is also showing positive changes and the government would work to further narrow the gender gap in this regard.

Meanwhile, the forum also touched upon the importance of establishing collaborative framework consisting of all stakeholders: the public sector, the private sector, development partners, the media and other stakeholders; that is believed to identify the policy, financial, logistics and other possible challenges the women may face as a result of the available gender gaps and discriminations and provide capacity building trainings and financial supplies that help ensure the keen participation of the women in the economy.

Some of the company owning women who have a bunch of experiences in the businesses, also shared their success stories.